ጥር፡ 4 ቀን 2003 ዓ.ም (12/1/2011)

ለመልአክ ጽዮን አባ ግርማ ከበደ
የርዕሰ/አ/ለ/ደ/ጽ/ቅ/ማርያም የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክን አስተዳዳሪ
ለንደን።

ጉዳዩ፤ የቤተክርስቲያናችን ገንዘብና ንብረት ይጠበቅ፣ ሥርዓትና ሕግ ይከበር የሚሉ ካህናትንና ምዕመናንን ለማስገለል የሚደረገውን ሕገወጥ ድርጊትና፤ ይህንንም ለማስፈጸም ሲባል በቤ/ክናችን ስለሚታየው የሕግና የሥርዓት አልበኝነት አሠራርን ይመለከታል።

ከዓራት ዓመታት በፊት ሁሉም ካህናትና ምእመናን የተስማሙበትን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ መመሪያዎ በማድረግ ሠርተው እንዲያሠሩ የአስተዳደር ኃላፊነቱን በእግዚአብሔርና በህዝቡ ፊት ቃል ገብተው መረከብዎ ይታወቃል። ይሁን እንጂ የገቡትን ቃል በመዘንጋት፤

1. አንዱ ከሌላው ልዩነት ሳይደረግበት ሁላችንም ሥርዓትና ሕግ አክብረን በቤ/ክችን በሰላምና በአንድነት ለማገልገልና ለመገልገል የሚያስችለንን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ተከትለው ባለመሥራትዎ፡ እርስዎም ሆኑ የሰ/መ/አ/ጉባኤ አባላት በውስጠ ደንቡ የተሰጣችሁን የ3 ዓመታት የስልጣን ዘመን ከህግ ውጭ በማራዘም አሁን 5ኛ ዓመታችሁን ከመያዛችሁም በላይ፥ የቤ/ክችንን ገንዘብና ንብረት ለማስጠበቅና ደንቡን ለማስፈጸም ከፍተኛ ኃላፊነት ያላቸውን ተቋማት (የቁጥጥር ኮሚቴ፣ የሕግና ሥነ ሥርዓት ጉባኤና የካህናት ጉባኤ) የተጣለባቸውን ኃላፊነት እንዳይወጡና በመጨረሻም እንዲፈራርሱ አድርገዋል፤

2. ሁሉንም ካህናትና ምእመናን በአንድነት፣ በሰላምና በእኩልነት መምራት ሲገባዎ፤ አንድ ዓይነት የፖለቲካ፣ የጥቅም ወይም የጎጥ ትስስር ካላቸው የተወሰኑ ካህናትና ምእመናን ጋር በመወገን፡ ሌሎቹን ካህናትና ምእመናን ከቤ/ክን አገልግሎት ለማስገለል በሚያደርጉት የመለያየት ተግባር በቤ/ክችን ካህናትና ምእመናን ዘንድ ሰላምና አንድነት እንዳይኖር አድርገዋል፤

3. የቤ/ክችን ገንዘብና ንብረት መባከንንና መዘረፍን አስመልክቶ በየጊዜው የሚቀረቡ የሙስና ጥያቄዎችና አቤቱታዎች አጣሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ እንዳይጣሩ ከማድረግዎም አልፎ፥ ጥያቄ በሚያቀርቡ ሰዎች ላይ የጥላቻና የውሸት ውንጀላ በማካሄድና ጥያቄዎችን በመሸፋፈን እስካሁን ድረስ ጥያቄዎቹ ሕጋዊ የሆነ መፍትሄ ሳያገኙ እንዲቆዩ አድርገዋል፤

4. የቤ/ክችን መሠረታዊ አቋም በመግለጫችን ገጽ 9 ተ.ቁ 2 ላይ እንደተገለጸው "የለንደን ደ/ጽ/ቅ/ማርያም ቤተክርስቲያን እያንዳንዱን ካህንና ምእመን በፖለቲካ አመለካከቱ፣ በጎሳው፣ በቋንቋውና፣ በትውልድ አካባቢው ምክንያት ምንም ዓይነት ልዩነት ሳታደርግ መንፈሳዊና ማህበራዊ አገልግሎቷን ለሁሉም በእኩልነት የምትሰጥና፥ ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት (ፓርቲ) ጋር የማትወግን መሆኗን ታረጋግጣለች" የሚልና፡ እንዲሁም ሕገ ቤተክርስቲያንን ተከትለው የማይሠሩና ሃብቷንና ንብረቷን ያለአግባብ የሚዘርፉና የሚያዘርፉ አባቶችን (ካህናትን) አሁንም ሆነ ለወደፊት የአባትነት እውቅና አትሰጥም በሚል በግልጽ ተቀምጦ እያለና፤ እርስዎም ይህንን አክብረው ማገልገል ሲገባዎት፣ ፍጹም ተቃራኒ በሆነ መልኩ "የቤ/ክችንን አቋም ስለማይቀበሉ" በሚል ቤ/ክችን ከእናት ቤ/ክን ለመገንጠል የሚያስችልና በብሪታንያ ከሚገኙ የኢ/ኦ/ተ/አብያተክርስቲያናት ጋር አንድነትና ግንኙነት እንዳይኖራት ሕገወጥ መመሪያ በማውጣት ቀኖና ቤ/ክንን ከመጣስዎም አልፎ፣ ቤ/ክችንን የተወሰኑ ግለሰቦች ብቻ የሚጠቀሙባት የግል ድርጅት እንድትሆን አድርገዋል፤

5. በተለይ ከዛሬ ነገ ከስህተትዎ ይታረሙ ይሆናል፣ የራሳችንን ጉዳይ እራሳችን መፍታት አለብን በሚል ከዚህ በፊት በፈጸሟቸው ሕገወጥ ድርጊቶች ሁሉ በሕግ ባለመጠየቅዎ፤

ሀ. «ከሰበካው መ/አ/ጉባኤ የተሰጠ ህጋዊ ውሳኔ» በሚል መስከረም 9 ቀን 2003 ዓ.ም በቤ/ክችን ማህተምና በፊርማዎ በማረጋገጥ ለዲያቆን ድርሻዬ ለማ ከማንኛውም የቤ/ክን አገልግሎትና የካህናት ጉባኤ አባልነት ታግደሃል የሚል ደብዳቤ በመስጠት፣ በውስጥ ደንቡ አንቀጽ 48 (1&2) የተደነገገውን በመጣስና የስልጣን ገደብዎን ባለማወቅ ለተጠቃሹ ካህንና፣ ከበስተጀርባ ሆነው ድርጊቱን ግፉበት ለሚሏዎት ቡድኖችና ግለሰቦች እንዲሁም ጉዳዩን በምስጢር ለሚከታተሉ የመንግስት ባለስልጣናት ጭምር በማስተላለፍዎ፣ ከላይ የጠቀስናቸውን ሕገወጥ ተግባርዎን ሁሉ በአዲስ መልክ የቀጠሉበት መሆኑን በግልጽ አረጋግጠዋል፤

ለ. ታህሳስ 3 ቀን 2003 ዓ.ም በተቀደሰው የቤ/ክን አውደ ምህረት ላይ ቆመው ከ18 ዓመታት በላይ ቤ/ክችንን ሲያገለግል የቆየውን የዲያቆን ድርሻዬ ለማን ስም ለማጥፋት ያቀርቡት የሃሰት ውንጀላ የቤ/ክችንን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 48 የጣሰ ብቻ ሳይሆን፣ ወንድማችን የፈጸመው ጥፋት እንኳን ቢኖር፣ በውስጠ ደንባችን መሠረት ጉዳዩ በደርጃ ሳይታይ፣ ለቤ/ክን ጉባኤ ያውም በቅዳሴ ለተሰበሰቡ ምእመናን አቅርበው ለመወንጀል መሞከርዎ፣ ለስጋዊ ፍላጎትዎ ሲሉ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል (ማቴ 18፡15) የካዱና ያዋረዱ መሆንዎን በግልጽ አሳይተዋል። ከዚህም ሌላ፤ ዲያቆን ድርሻዬን በተመለከተ አንድም ቀን በአጀንዳ ለውይይት ቀርቦ በካህናት ጉባኤ የተወያየንበት ጊዜ ሳይኖርና እንዲሁም ከላይ እንደገለጽነው ብዙዎቹ ንዑሳን ኮሚቴዎች ሥራቸውን እንደማይሠሩና እየሠራን ነው የሚሉትም (የሕንጻና ልማት ኮሚቴ አባላት) የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸው መሆኑ እየታወቀ ፣ የካህናት ጉባኤና የጥምር ጉባኤ በተጠቀሰው ወንድማችን ላይ ተወያይቶ ወሰኗል የሚል የውሸት መግለጫ መስጠትዎ በጣም አሳፋሪና ፈጽሞ የሃይማኖት አባት አለመሆንዎን የሚያሳይ ድርጊት ሆኖ አግኝተነዋል።

ሐ. ቤ/ክችን ካህናቱንም ሆነ ምእመናኑን የምታስተዳድርበትና ቅሬታ ቢኖራቸውም የምታስታርቅበት ሥርዓትና ሕግ እያላት፣ ይህንኑ ሥርዓትና ሕግ ተከትለው መሥራትና ማሠራት ባለመቻልዎ፣ ከካህናትም ሆነ ከምእመናን የሚቀርቡ አቤቱታዎች ህጋዊና ተገቢ ውሳኔ ሊያገኙ ባለመቻላቸው፣ አንዳንድ ካህናትና ምእመናን አቤቱታቸውን ወደ ውጭ ህጋዊ አካል ለማቅረብ የተገደዱ መሆናቸው ለሁሉም ያደባባይ ሚስጢር ነው። ለምሳሌ፤ በቅርብ ጊዜ የቤ/ክችን ምእመን የሆኑ እናት ተበድያለሁና በቤ/ክን ሥርዓትና ሕግ ይታይልኝ በማለት በአንድ ካህን ላይ ያቀረቡትን አቤቱታ በተገቢው መንገድ እንዲታይና የሁሉንም መብት በመጠበቅ ተገቢውን ቅጣት (ንስሐ) በመስጠት እርቀሰላም እንዲወርድ ባለማድረግዎ ምክንያት፣ ክርስቶስ የሞተላት ምእመን እንድትጠፋ አድርገዋል። በካህናት ጉባኤ መታየት የሚገባውንም የካህኑም ጉዳይ ሳይታይ ወደ ፖሊስ እስከመሄድ ደርሶ ቤ/ክችን ድብቅ ወንጀል የሚፈጸምባት ቦታ ናት ተብላ እንድትመዘገብና በጥያቄ ምልክት ውስጥ እንድትቀመጥ በማድረግዎ ከፈጸሟቸው ሕገወጥ ድርጊቶች ሁሉ ከፍተኛ ሆኖ አግኝተነዋል።

ስለዚህ፤ ከዚህ በፊት በሕግና ሥነሥርዓትና በካህናት ጉባኤ በተደጋጋሚ የተሰጠዎትን ማሳሰቢያና የማስጠንቀቂያ ምክር ተግባራዊ አለማድረግዎን እያስታወስን፣ አሁንም በድጋሚ አጥብቀን ልንመክርዎና ልናስጠነቅቅዎ የምንፈልገው፡ ከዚህ በላይ በተገለጹትም ሆነ ባልተገለጹት ሕገወጥ ድርጊትዎ ምክንያት፤

1. በደል የተፈጸመባቸው ካህናትና ምእመናን እርስዎን ወደሕግ ለማቅረብ ከመገደዳቸው በፊት፣ አማራጭ የሌለው መፍትሄ በእምነታችን መመሪያ (ማቴ 5፡23) መሠረት፣ ለፈጸሟቸው ስህተቶች ሁሉ ነገ ዛሬ ሳይሉ በደል በፈጸሙባት የቤ/ክን አውደምህረት ላይ ይቅርታ በመጠየቅ እራስዎንም ሆነ በደል የተፈጸመባቸው ካህናትንና ምእመናን ለማዳን እንዲችሉ፤
2. የሰበካው መ/አ/ጉባኤ አባላት ምርጫ በሕጉ መሠረት በአስቸኳይ እንዲካሄድ፤
3. በግልጽም ሆነ በስውር የባከነውንና የተዘረፈውን የቤ/ክችንን ገንዘብና ንብረት የሚያጣራ አጣሪ ኮሚቴ በጠቅላላው ጉባኤ እንዲቋቋም እንዲያደርጉና ተፈጸመ የሚባለው ሙስና ሁሉ ተጣርቶ ለህዝብ ግልጽ እንዲሆን፤
4. በቤ/ክችን የሕግና የሥርዓት አልበኝነት አሠራር ሊሰፍን የቻለው የቁጥጥር ኮሚቴ፣ የሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤና የካህናት ጉባኤ በውስጠ ደንቡና በጠቅላላው ጉባኤ የተሰጣቸውን ኃላፊነት እንዳይወጡ በመደረጉ ስለሆነ፤ ጠቅላላው ጉባኤ ተጠርቶ በአስቸኳይ የተጠቀሱትን ተቋማት (ኮሚቴዎች) በአዲስ መልክ በማቋቋም የሕግና የሥርዓት አልበኝነት አሠራር ባስቸኳይ እንዲቆም እንዲደረግ፤

5. በቤ/ክችን ሥርዓትና ሕግ አቤቱታቸው ሳይታይላቸው በመቅረቱ ለፖሊስ እንዲያመለክቱ የተገደዱት ምእመን ጉዳይ በውስጠ ደንባችን መሠረት ገለልተኛ በሆኑ የካህናት ጉባኤ አባላት በአስቸኳይ እንዲጣራና ቤ/ክችን ወንጀል የሚፈጸምባት ሳትሆን የይቅርታና የሰላም ቦታ መሆኗ ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል እንዲረጋገጥ፤
6. ቤ/ክችን በኢ/ኦ/ተ/ቤክን ቅዱስ ሲኖዶስ ሥር የምትመራ ለመሆኑ በውስጥ መተዳደሪያ ደንባችንም ሆነ በፓትርያርኩ ላይ ባወጣነው መግለጫ በግልጽ የተደነገገ መሆኑ እየታወቀ፣ ከሌሎች የኢ/ኦ/ተ/አብያተክርስቲያናት ጋር አንድነትና ግንኙነት አይኖራትም በሚል ያውጡት ሕገወጥ መመሪያ የውስጥ ደንባችንንም ሆነ፣ የቤ/ክችንን ቀኖና የሚቃረን ከፍተኛ ክህደት በመሆኑ፤ በኢ/ኦ/ተ/ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ሥር በሚገኙ አብያተክርስቲያናት ማገልገል እንዳይችሉ እስከመወገዝ የሚያደርስዎ ስለሆነ፤ በጽሁፍ ያስተላለፉተን ሕገወጥ መመሪያ ስህተት መሆኑን አምነው በአስቸኳይ እንዲያነሱ፤ በማለት የማስጠንቀቂያ ምክራችንን እየሰጠን፥ አሁንም ከስህተትዎ የማይታረሙና ከዚህ በላይ ያቀረብንልዎትን የመፍትሄ ሃሳቦች ይህ ደብዳቤ በደረሰዎ በ14 ቀናት ውስጥ ተግባራዊ የማያደርጉ ከሆነ ግን፤ በእያንዳንዱ ግለሰብም ሆነ በቤ/ክችን ላይ ለፈጸሙትም ሆነ ለሚፈጽሙት ሕገወጥ ድርጊት ሁሉ በሚመለከተው የሃገሪቱ ሕግ ከመጠየቅ (ከመክሰስ) በስተቀር ሌላ አማራጭ የሌለ መሆኑን እንዲያውቁት በጥብቅ እናሳስብዎታለን።

እግዚአብሔር ቤተክርስቲያናችንን ይጠብቅልን!!

<u>ግልባጭ፤</u>
ለባተርሲ ፖሊስ ጣቢያ።

<u>ከርዕሰ/አ/ለ/ደ/ጽ/ቅ/ማርያም የኢ/ኦ/ተ/ቤተክርስቲያን ካህናትና ምእመናን</u>

| ተ.ቁ (No) | ስም (Name) | ፊርማ (Signature) |
|---|---|---|
| 1 | Rev. MULUBHAN Sixpun J. | [signature] |
| 2 | Merigeta. M. Kemnow | [signature] |
| 3 | A. Deacon. D. Dinkevu | |
| 4 | Deacon S. Chala | [signature] |
| 5 | Deacon Y. Woldesube | [signature] |
| 6 | Deacon. Y. Worde | [signature] |
| 7 | Deacon. D. Debella | |
| 8 | Merigeta G.S. Abay | |
| 9 | Deacon D. Lemma | [signature] |
| 10 | Y. MR [signature] | |
| 11 | Mr. Y. Yemer | [signature] |
| 12 | | |
| 13 | | |